በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን በድርድር ሽያጭ ወደ ግል ይዞታ ስለማዛወር የአፈፃፀም መመሪያ

512/2013

ነሃሴ 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

መግቢያ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ይዞታ ለማዛወር በድርድር የሚፈጸም ሽያጭ ከፕራይቬታይዜሽን ስልቶች አንዱ ስለሆነ ወደ ግል ይዞታ የሚተላለፉ የልማት ድርጅቶች የአፈፃፀም ሥርዓት በግልጽነት መርህ ላይ የተመሰረተ መሆን እንደሚገባው የተደነገገ በመሆኑ፤

ወጥ የሆነ የመንግሥትን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል በግልጽነትና በተጠያቂነት መንፈስ የሽያጭ ድርደሩን ሂደት ለማስኬድ የሚያግዝ የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916 /2008 አንቀጽ 31 (ለ)(9) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. የመመሪያው ስያሜ

ይህ መመሪያ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን በድርድር ሽያጭ ወደ ግል ይዞታ ስለማዛወር የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር **512/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

2.1. “ሚኒስቴር እና ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ማለት ነው።

2.2. “የልማት ድርጅት” ማለት የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር 146/1991 አንቀጽ 2 (2) ሥር የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

2.3. “አክሲዮን ማህበር” ማለት በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት ባለቤትነት የተያዘ አክሲዮን ማህበር ነው።

2.4. “የድርድር ሽያጭ ” ማለት አንድን የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም አክስዮን ማህበር ወይም የአክሲዮን ድርሻ ወይም ቅርንጫፍ በድርድር የሁለት ወገኖችን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ በመጨረሻ ስምምነት የሚያደርስበት የሽያጭ ስልት ነው።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Public Enterprises

3. በድርድር ሽያጭ ስልት መጠቀም የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ የድርድር ሽያጭ ስልትን በመጠቀም የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፤ አክሲዮን ማህበራትን፡ የአክሲዮን ድርሻ እና/ወይም ቅርንጫፎቻቸውን ወደ ግል ይዞታ ለማዛወር ይችላል።

3.1. ሶስት ጊዜ ለጨረታ ቀርቦ ወደ ግል ባለሀብት ሊተላለፍ ያልቻለን የልማት ድርጅት ወይም አክሲዮን ማህበር በድርድር እንዲሸጥ ሲወሰን ወይም

3.2. የልማት ድርጅቱ ወይም የአክስዮን ማህበሩ ባለበት ሁኔታ የማይቀጥል መሆኑ ሲታመንበት እና በድርድር መሸጥ ከሌሎች አማራጮች የተሻለ ነው ተብሎ በሚኒስትሩ ሲወሰን በድርድር ሊሸጥ ይችላል።

4. የድርድር ሽያጭ መርሆዎች

የድርድር ሽያጭ ኮሚቴው በማንኛውም የድርድር ሂደት የሚከተሉትን መርሆዎች መከተል አለበት፣

4.1. በሌሎች ህጎች ወይም በዚህ መመሪያ በግልጽ ካልተቀመጠ በቀር ማንኛውም ተደራዳሪ በዜግነት ወይም ከመደራደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግሥት የልማት ድርጅቶች የድርድር ሽያጭ እንዳይሳተፉ አለመከልከል ወይም አድል አለማድረግ፤

4.2. ከመንግሥት ልማት ድርጅቶች ወይም አክሲዮኖች እና ቅርንጫፎቻቸው የድርድር ሽያጭ አፈፃፀም ጋር በተያዘ የሚሰጡ ውሣኔዎች እና የሚወሰዱ እርምጃዎች ሀላፊነትንና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ መፈጸም ፣

4.3. በማንኛውም የድርድር ሂደት የተደራዳሪዎች እራሳቸው ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በአካል መገኘት ይኖርባቸዋል።

4.4. የድርድር ኮሚቴው አባላት የድርድሩን ሂደት እና ውጤቱ ሚስጥራዊነት ውጤቱ በይፋ እስኪገለጽ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Public Enterprises

4.5. ከአንድ በላይ ተደራዳሪዎች በቀረቡ ጊዜ ኮሚቴው ተደራዳሪዎችን በተናጠል ማደራደር ይኖርበታል።

5. የድርድር ሽያጭ ስልት ስለሚፈቀድባቸው ድርጅቶች ዝርዝር

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 የተመለከቱትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ በድርድር እንዲሸጡ የተለዩ የልማት ድርጅቶች ዝርዝር በሚኒስትሯ/ሩ ይፀድቃል።

ክፍል ሁለት

የድርድር ሽያጭ ኮሚቴ አሰያየም እና ስልጣንና ተግባር

6. የድርድር ሽያጭ ኮሚቴ መሰየም

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የድርድር ሽያጭ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ መሰረት ተሰይሟል።

7. የድርድር ሽያጭ ኮሚቴ አባላት

7.1. የድርድር ሽያጭ ኮሚቴው በሚኒስትሯ/ሩ የሚሰየሙ ከ5 ያላነሱ አባላት ይኖሩታል።

7.2. የኮሚቴው አባላት የሚሰየሙት ለአንድ የድርድር ሽያጭ ለማስፈጸም ብቻ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በድጋሚ በሚኒስትሯ/ሩ ሊሰየሙ ይችላሉ።

7.3. በንኡስ አንቀጽ 7.1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኮሚቴው ፀሐፊ በኮርፖሬት ፋይናንስ እና አስተዳደር ዘርፍ አቅራቢነት በሚኒስትሯ/ሩ የሚሰየም ይሆናል።

8. የድርድር ሽያጭ ኮሚቴው ተጠሪነት

የድርድር ሽያጭ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሯ/ሩ ይሆናል።

9. የድርድር ሽያጭ ኮሚቴው አባላት አሰያየም እና መመዘኛዎች

9.1. የኮሚቴው አባላት ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች መካከል የሚሰየሙ ይሆናሉ፡፡

9.2. ማንኛውም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሰራተኛ በድርድር ሽያጭ ኮሚቴ አባልነት ሊሰየም የሚችለው የሚከተሉትን መመዘኛዎች ያሟላ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

ሀ. በትምህርት ዝግጅትዋ/ቱ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላት/ያለው፤

ለ. በተመደበችበት/በት የስራ ክፍል ግንባር ቀደም ሰራተኛ መሆንዋ/ኑ የተረጋገጠ ሲሆን እና የድርድር ክህሎት፤ ሃሳብን የመግለጽ እና የማሳመን ብቃት ያላት/ያለው፤

ሐ. ከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት የሚሰማት/የሚሰማው፤

መ. ከሙስና እና ከኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ጽዱ የሆነ/ች እንዲሁም በመልካም ሥነ-ምግባር የታነጸች/የታነጸ፤

ሠ. ለድርድር ሽያጭ የቀረቡ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ወይም አክሲዮን ማህበራትን ለሽያጭ ለማቅረብ በተደረገዉ የዋጋ ትመና ሥራ ዉስጥ ያልተሳተፈች/ያልተሳተፈ እና

ረ. የድርድር ሽያጭ ኮሚቴ አባላት ስየማ ከመደረጉ በፊት ባሉት ሁለት አመታት በማንኛውም የዲስፕሊን ጉድለት ተከሳ/ሶ ያልተቀጣች/ያልተቀጣ መሆን ይኖርባታል/ይኖርበታል፡፡

10 የድርድር ሽያጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

10.1. የድርድር ሽያጭ ኮሚቴው በተደራዳሪዎች የቀረበው የድርድር ፕሮፖዛል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፤

10.2. የድርድር ኮሚቴው ድርድሩ የሚካሄድበትን ሂደት የሚገልጽ መርሃ ግብር ያዘጋጃል፡፡ በሚኒስትሯ/ሩ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

10.3. ኮሚቴው ለድርድሩ ስራ ስኬት አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን እንደአስፈላጊነቱ ለድርድር ሽያጭ የቀረበውን ድርጅት በመጎብኘት የተሟላ መረጃ ሊያገኝ ይችላል፤

10.4. ኮሚቴው ምክርና የባለሙያ እገዛ በሚፈልግበት በማንኛውም ጊዜ መጠየቅና ማግኘት አለበት፡፡ ምክርና የሞያ እገዛውን መስሪያ ቤቱ በራሱ ሰራተኞች ሊሰጥ ባልቻለ ጊዜ ከመስሪያ ቤቱ ውጭ የሆነ ባለሞያ እንዲመደብለት ለሚኒስትሯ/ሩ ጥያቄ ያቀርባል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Public Enterprises

10.5. ኮሚቴው ድርድር ሲያካሂድ የሚከተሉትን እንደ መስፈርት ይጠቀማል፡፡

ሀ. የመደራደሪያ ዋጋ

ለ. የአከፋፈል ሁኔታ እና

ሐ. ተደራዳሪዎች የወደፊት የስራ ዕቅድ

መ. ተደራዳሪው በዘርፉ ያለው የስራ ልምድና

10.6. የድርድሩ ውስብስብነት እና የተደራዳሪዎቹ ብዛት ካላገደው በስተቀር ኮሚቴው ድርድሩን ከ15 የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

10.7. ኮሚቴው የደረሰበትን የድርድር ሽያጭ ውሳኔ ሃሳብ ከሶስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሚኒስትሯ/ሩ ያቀርባል፡፡

10.8. በሚኒስትሯ/ሩ በጽሁፍ ካልፀደቀ በስተቀር ኮሚቴው ያቀረበው የድርድር ሽያጭ ውሳኔ ሃሳብ የመጨረሻ ውጤት ተደርጎ አይወሰድም፡፡

11 የኮሚቴው ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

የኮሚቴው ሰብሳቢ የሚከተሉት ቷግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል

11.1. የኮሚቴውን የስብሰባ ጊዜ ሰሌዳ እንዲዘጋጅ በማድረግ ስብሰባዎችን በጊዜው ይጠራል፤

11.2. የኮሚቴውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፤

11.3. የድርድር ኮሚቴው አጠቃላይ ስራ በዚህ መመሪያ መሰረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፤

11.4. የኮሚቴውን ውሳኔ ሃሳብ የያዘ ሪፖርት ከቃለ ጉባኤ ጋር ለሚኒስትሯ/ሩ ያቀርባል፤

12 የኮሚቴው ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

የኮሚቴው ፀሐፊ የኮሚቴው አባል ሲሆን የሚከተሉት ተግባራትና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

12.1. የመደራደሪያ ሰነድ የሚገዙትን ወይም በድርድሩ የሚሳተፉትን ሰዎች/ ተቋማት ዝርዝር መዝግቦ ይይዛል፤ በድርድር መክፈቻው እለትም ለማመሳከሪያ ያቀርባል፤

12.2. ማናቸውንም የድርድር ሰነድ ድርድሩ ተጠናቅቆ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስትሯ/ሩ እስኪቀርብ ድረስ በዚህ መመሪያ መሠረት አሟልቶ ይይዛል፡፡

12.3. የስብሰባ አጀንዳ ያሰራጫል፤

12.4. የኮሚቴውን ስብሰባዎችና ውይይቶች ቃለ ጉባዔዎች አዘጋጅቶ በማስፈረም ይይዛል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም እንዲደርስ ያደርጋል፣

12.5. የድርድሩን የተጠቃለለ ሪፖርት ያዘጋጃል፤ ይይዛል።

13 የሰብሳቢው ወይም የፀሐፊው በድርድሩ አለመገኘት

13.1. ሰብሳቢው በድርድሩ ለመገኘት ባልቻለ ጊዜ ይህንኑ ለሚኒስትሯ/ሩ በማሳወቅ ጊዜያዊ ሰብሳቢ ከኮሚቴው አባላት ወይም አባል ካልሆኑ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች መካከል እንዲመደብ ያስደርጋል።

13.2. ፀሐፊው በድርድሩ መገኘት ባልቻለ ጊዜ ኮሚቴው ጊዜያዊ ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል መድቦ ሥራውን ይቀጥላል።

14 ምልዓተ-ጉባዔ እና የውሣኔ አሰጣጥ

14.1. ከኮሚቴው የድርድር ስራውን የሚያካሂደው ከአባላቱ መካከል ሁለት ሦስተኛው ተገኝተው ምልዓተ-ጉባዔ ሲሟላ ነው።

14.2. የኮሚቴው የውሣኔ ሃሳብ የሚባለው በድርድሩ ከተገኙት የኮሚቴው አባላት የአብላጫ ድምጽ ያገኘው ሃሳብ ነው። ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ድምጽ የኮሚቴው የውሣኔ ሃሳብ ሆኖ ይቆጠራል።

14.3. በአብላጫ ድምጽ ድጋፍ ባገኘው የውሳኔ ሃሳብ ያልተስማማ የኮሚቴው አባል የልዩነት ሃሳቡን በቃለ ጉባኤ እንዲሰርፍለት ሊጠይቅ ይችላል።

15. የድርድር ሽያጭ ኮሚቴ አባላት ሥነ-ምግባር

15.1. የድርድር ኮሚቴው አባል ከተደራዳሪዎች ወይም ከወኪሉ[illegible]ታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገንዘብም ሆነ በዓይነት ምንም ዓይነት ስጦታ መቀበል የለበትም።

15.2. ማናቸውም የኮሚቴው አባል በሚኒስትሯ/ሩ በጽሁፍ ካልተፈቀደለት በስተቀር በእጁ የሚገኘውን መረጃ ወይም ከርድሩ ጋር በተያያዘ የሚያውቀውን ማናቸውንም ሚስጢር ማሳወቅ አይችልም፡፡

16 የጥቅም ግጭት

16.1. ማንኛውም የድርድር የኮሚቴ አባል በድርድር ኮሚቴው መሳተፉ እና ውሳኔ መስጠቱ ራሱን ወይም ቤተሰቡን ሊጠቅም የሚችል መሆኑን ሲረዳ፤ የጋብቻ፤የደም ወይም ሌላ ማናቸውም በገለልተኝነቱ ላይ ተፅእኖ የሚፈጥር ግንኙነት ሲኖረው፤ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት የጥቅም ግጭት የሚፈጠርና ትክክለኛና ፍትሐዊ አቋም ለመያዝ የማያስችለው ሁኔታ ሲከሰት ይህንኑ ለሚኒስትሯ/ሩ እና ለሰብሳቢው በጽሁፍ በማሳወቅ ራሱን ከኮሚቴ አባልነት ማግለል አለበት፡፡

16.2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 1 የተገለጸው የጥቅም ግጭት በሰብሳቢው ላይ ሲከሰትም ሰብሳቢው ይህንኑ ለሚኒስትሯ/ሩ በጽሁፍ በማሳወቅ ራሱን ከኮሚቴው ማግለል አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ ሚኒስትሯ/ሩ የኮሚቴውን ሰብሳቢ ይሰይማሉ፡፡

16.3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተደራዳሪዎቹ መካከል የኮሚቴው አባል ወይም ሰብሳቢ በድርድሩ በገለልተኝነት ሊሳተፍ አይችልም የሚል ቅሬታ ወይም ጥቆማ የቀረበ እንደሆነ ጥቆማ የቀረበበት የኮሚቴው አባል ወይም ሰብሳቢ አቤቱታ በቀረበበት ድርድር ላይ እንዳይሳተፍ ሚኒስትሯ/ሩ ሊወስኑ ይችላል፡፡

16.4. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው ተግባሩን በገለልተኝነት እና በፍትሃዊነት አይወጣም ተብሎ ሲታመን ሙሉ በሙሉ በሌላ ኮሚቴ በሚንስትሯ/ሩ ሊተካ ይችላል፡፡

17 የኮሚቴው አባላት ተጠያቂነት

17.1. በዚህ መመሪያ የተካተቱ ጉዳዮችን ተላልፎ የተገኘ የድርድር ሽያጭ ኮሚቴ አባል በህግ አግባብ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

17.2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 1 መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃ መወሰዱ ሊኖር የሚችለውን የወንጀል ተጠያቂነት አያስቀረውም፡፡

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Public Enterprises

ክፍል ሦስት

የድርድር ሽያጭ ሰነድ ዝግጅትና ስለድርድር ማስታወቂያ

18 የድርድር ሽያጭ ሰነድ ዝግጅት

18.1. የድርድር ሽያጭ ሰነድ የሚዘጋጀው በኮርፖሬት ፋይናንስ እና አስተዳደር ዘርፍ ነው።

18.2. ለድርድር ሽያጭ የተዘጋጀው ሰነድ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማህተም ያረፈበት መሆን አለበት።

18.3. የሚዘጋጅ የድርድር ሽያጭ ሰነድ ተደራዳሪዎች የሚያቀርቡትን የድርድር ሃሳብ እና ፍላጎት በአግባቡ ሞልተው ማቅረብ እንዲችሉ ግልጽ ሆኖ፣ ተገቢና የተሟላ መረጃ መያዝ ይኖርበታል።

18.4. ሰነዱ ለድርድር ሽያጭ የቀረበውን ድርጅት ስምና አድራሻ፣ ዜግነት፣የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ፣ የታደሰ የንግድና ኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የመጨረሻ በጀት አመት ሰው ኃይል ሁኔታ መረጃ፣ ያለፉት 3 ተከታታይ ዓመታት በኦዲተር የተመረመሩ የሂሳብ መግለጫዎች እና በዘርፉ ያለው ልምድ መግለጽ አለበት።

18.5. ወቅታዊ የሆኑ የድርጅቱ ኦፕሬሽናል ስራዎች አፈፃፀም መረጃ መግለጽ አለበት።

18.6. የቋሚ ንብረቶች ዝርዝር ሁኔታ በመጠን፣ በዓይነትና በእድሜ ተለይቶ መገለጽ አለበት።

18.7. የውል ናሙና፣ የማወዳደሪያ መስፈርቶችና የምዘና ሁኔታ፣የምርጫ ቅድሚያ የሚያስገኙ ጉዳዮች ማካተት አለበት።

18.8. እንደዚሁም የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ (Bid Form) መያዝ አለበት።

19. የድርድር ማስታወቂያ ይዘት

የድርድር ሽያጭ ማስታወቂያ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል።

19.1. ለድርድር የቀረበውን ድርጅት ስም እና አድራሻ፣

19.2. የድርድር ሽያጭ ሰነዱን መስሪያ ቤቱ መሸጥ የሚጀምርበትን ቀን፣ የሰነዱ መሸጫ ዋጋ እና ሰነዱ የሚገኝበትን ቦታ፣

19.3. የድርድር ሽያጭ ሰነዱን ማስገባት የሚያበቃበት ቀን፣ የድርድር ሰነዱ የሚከፈትበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ፣

19.4. ተደራዳሪዎች የጨረታውን ሰነድ ሞልተው ሲያቀርቡ የታደሰ የንግድ ፈቃድ አያይዘው ማቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ መግለጫ እና

19.5. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የድርድር ሽያጩን በከፊል ወይም በሙሉ ለመሠረዝ መብት ያለው ስለመሆኑ የሚያስታውቅ መግለጫ መያዝ አለበት፡፡

20. የድርድር ማስታወቂያ ስለማውጣት

20.1. ሚኒስቴሩ በአንቀጽ 4 መሰረት በድርድር ሲሸጥ የሚፈልጋቸውን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወይም አክሲዮን ማህበራት ተደራሽ በሆኑ በመገናኛ ብዙሃን፤ በራሱና በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ድህረ ገጽ ይፋ ያደርጋል፡፡

20.2. የመጀመሪያ የድርድር ማስታወቂያ ለ60 (ስልሳ) ቀናት በአየር ላይ ይቆያል፡፡

20.3. በመጀመሪያ የድርድር ማስታወቂያ መሰረት ተደራዳሪ ካልቀረበ በድጋሚ የድርድር ጨረታ ማስታወቂያው ለ30 (ለሳሳ) ቀናት በአየር ላይ ይቆያል፡፡

21. በተደራዳሪዎች መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮች

በተደራዳሪዎች የሚቀርብ የድርድር ሰነድ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

21.1. አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ የሚቀርበው የድርድር ሰነድ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

21.1.1. የአመልካቹን ሙሉ ስም፤ አድራሻ እና ዜግነት፤

21.1.2. የተሰማራበትን የሥራ ዘርፍ፤

21.1.3. ለመግዛት የሚፈልገው የልማት ድርጅት ወይም አክስዮን ማሕበር ስም፤

21.1.4. ለመግዛት የተፈለገው የአክሲዮን ድርሻ ከሆነ የአክሲዮን ማህበሩን ስምና የሚገዛውን የአክሲዮኖች ብዛት፤

21.1.5. የግዥውን ዋጋ ለመክፈል የሚያስፈልገው ገንዘብ የሚገኝበትን የፋይናንስ ምንጭ፤

21.1.6. የሚደራደርበትን የገንዘብ መጠን፤

21.1.7. የወደፊት የስራ ዕቅድ መያዝ አለበት፡፡

21.2. አመልካቹ የንግድ ማሕበር ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 1 ስር ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሚቀርበው የድርድር ሰነድ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Public Enterprises

21.2.1. የታደሰ የንግድ ፈቃድና የምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

21.2.2. የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣

21.2.3. የመጨረሻዎቹ ተከታታይ ሶስት ዓመታት የሂሣብ መግለጫዎች (የሃብትና ዕዳ መግለጫ፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ ፣የጥሬ ገንዘብ ፍሰት) የሚገልጽ ማስረጃ እና

21.2.4. ግዥውን ለመፈፀም ከማህበሩ ባለቤቶች ወይም አስተዳዳሪዎች የተሰጠ የውሳኔ ቃለ ጉባኤ ወይም ደብዳቤ የያዘ መሆን አለበት፡፡

22. የድርድር ሰነድ ከተደራዳሪዎች ስለመቀበል

22.1. የተዘጋጀው የድርድር ሽያጭ ጥያቄ መቀበያ ሳጥን በማስታወቂያው ከተገለጸው የሰነድ ማስገቢያ የመጀመሪያው ቀንና ሰዓት ጀምሮ እስከ መጨረሻው የመዝጊያ ቀንና ሰዓት ድረስ ክፍት ሆኖ መገኘት ይኖርበታል፡፡

22.2. የድርድር ሰነድ የሚቀርበው ለዚሁ በተዘጋጀውና በኮሚቴ አባላት ባዶ መሆኑ ተረጋግጦ በታሸገ ሣጥን ውስጥ በመክተት ነው፡፡

22.3. የድርድር ሽያጭ ጥያቄ መቀበያ ሳጥኑ እስከሚከፈት ድረስ ቁልፉ በድርድር ኮሚቴው ፀሀፊ ተይዞ መቆየት ይኖርበታል፡፡

22.4.ማንኛውም የድርድር ሰነድ በተዘጋጀው ሳጥን ገቢ መደረግ አለበት፡፡ ሆኖም ግን የቀረበው የድርድር ሰነድ በተዘጋጀው የድርድር ጥያቄ መቀበያ ሳጥን ውስጥ ሊገባ የማይቻል ጥቅል የሆነ እንደሆነ ሰነዱ ለኮሚቴው ፀሐፊ በእጅ ይሰጣል፡፡ ፀሐፊው ስለተረከበው ሰነድ ሰነዱ በእጁ የገባበትን ቀንና ሰዓት የሚገልጽ ማረጋገጫ ለድርድር መጠየቂያ ሰነድ አስገቢው መስጠት አለበት፡፡

22.5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 4 መሰረት ፀሐፊው የተረከበውን ሰነድ በመክፈቻው ሥነ ሥርዓት ላይ ለሚገኙት የኮሚቴ አባላት ይገልጻል፡፡ የድርድር ሰነዱም ከሌሎች የድርድር ሰነዶች ጋር አብሮ እንዲከፈት ያቀርባል፡፡

22.6. የድርድር ሽያጭ ሰነዱ የሚከፈተው ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት የኮሚቴ አባላት ሲገኙ ነው፡፡

22.7. የድርድር ሽያጭ ሰነዱ በሚከፈትበት እለት የተደራዳሪዎች መገኘት አስፈላጊ አይደለም፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Public Enterprises